# የMCPS ስርአተ ትምህርት 2.0 (MCPS CURRICULUM 2.0)

**ተማሪዎችን ማጠናከር • ይዘትን ማገናኘት • ፈጠራን መንከባከብ**

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

በያዝነው አመት፣ ስርአተ ትምህርት 2.0 በMontgomery County Public Schools ከሙአለህፃናት እስከ 5ኛ ክፍል ድረስ ባሉ የመማርያ ክፍሎች ተግባራዊ ይሆናል። ስርአተ ትምህርት 2.0 የተተለመው ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የአካዴሚ ትምህርት ማግኘታቸውን ላማረጋገጥ ሲሆን፣ በተጨማሪም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጓቸውን ሙያዎች ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ነው.።

በአለም አቀፍ ደረጃ ግፊት የሚደረግባቸውን የሂሳብ፣ የንባብ፣ እና የፅሁፍ አዳዲስ መመዘኛዎች

ልጅን በሞላ የማስተማር ተሃድሶ ያለው ትኩረት

- በራስ መተማመንን እና ስኬትን የሚገነቡ ሞያዎች የሚኮተኩት።
- ተማሪዎችን በንባብና በሂሳብ ከመኮትኮት ባሻገር በሳይንስ፣ በማህበራዊ ጥናቶች፣ በመረጃ መሰረተ ትምህርት፣ በኪነጥበብ፣ በሙዚቃ፣በአካል ማጠንከርያ፣ እና በጤና የላቀ ጉጉት የሚለኩስ።

አስተሳሰብን፣ ማውጠንጠንን፣ እና ፈጠራን ለእድሜልክ ትምህርት የሚያቀናጅ።

- ርእሶችን በማቆራኘት ትምህርትን ያሚያጎለምስ

በተሻሻለ "መመዘኛውን በጠበቀ" ሪፖርት ካርድ የተማሪን ግስጋሴ የሚያስታውቅ

- ከክፍል ደረጃ ከሚጠበቀው አንፃር ተማሪው ምን እንደሚያውቅና ምን ማድረግ እንደሚችል ለወላጆች ተጨማሪ መረጃዎች ያቀርባል።

## የMCPS ስርአተ ትምህርት 2.0

የተገነባው ተማሪዎች ለእድሜ ልክ ትምህርት በሚገባ እንዲዘጋጁ የተማሪዎችን ሂሳዊና የፈጠራ አስተሳሰብ፣ እንዲሁም ተፈላጊ የአካዴሚያዊ ስኬት ችሎታዎችን በማዳበር ዙርያ ነው። ተማሪዎችንና መምህራንን ይበልጥ ለመጥመድና እንደ ኪነጥበባት፣ ጤና፣ የመረጃ መስረተ ትምህርት፣ ሳይንስ፣ ማህበራዊ ጥናቶች፣ እና የአካል ማጠንከርያ ትምህርት በመሳሰሉት የበለጠ ግዜ እንዲያሳልፉ ለማድረግ እንዲቻል የMCPSን የኤሌሜንታሪ ክፍሎች ስርአተ ትምህርትን አሻሽለነዋል። እነዚህን የትምህርት ርእሶች ከንባብ፣ ፅሁፍ፣ እና የሂሳብ አይነተኛ የይዘት መስኮች ጋር በማዋሃድ፣ በኤሌሜንታሪ ደረጃ የተደላደለ መስረት ለመገንባት እንዲቻል ተማሪዎች በሁሉም ርእሶች ጠንካራ፣ አመርቂ ትምህርት ይቀበላሉ።




ተጨማሪ ለማወቅ—
www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/2.0/

ትርጉም በLASU • Division of ESOL/Bilingual Programs • OCIP
© 2013 MCPS, Rockville, Maryland 0043.14 • EGPS • 7.13 • NP • Amharic